# የተሻሻለ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ

## (ረቂቅ ድንጋጌዎች ሀተታ ዘ-ምክንያት)


አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት፡- ዳኛ መሐመድ አህመድ (ሰብሳቢ)

ሸኽ መሐመድ ሀሚዲን (ዶ/ር) (አባል)

ዳኛ ሀሰን ታደሰ (አባል)

ሸኽ አህመድ አደም (ዳኛ)(አባል)

አቶ ኑረዲን ከድር (አባል)

አቶ አብዱልሀኪም ጀማል

አቶ ሻረው ዘለቀ (ጸሐፊ)



**የካቲት 2018**

# በረቂቅ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ዙሪያ የተዘጋጀ አጭር ማብራሪያ እና ሀተታ ዘምክንያት

በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር፣የአገልግሎት አሰጣጥ እና ተያያዥ ችግሮችን በዘላቂነት ስለሚፈታበት አግባብ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንዲመለክትላቸው በቁጥር ጠ/ም/0147/21/35/16 በቀን 14/8/2016 በተፃፈ ደብዳቤ በጠየቁት መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ፕሬዚዳንት አምስት አባላት ያሉት የኮሚቴ አባላትን በማዋቀር በፌ/ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል የጥናት ሰነድ እንዲዘጋጅ በተደረገው መሰረት የኮሚቴ አባላቱ ወደ ሥራ በመግባት በፍርድ ቤቱ የህግ ማዕቀፍ፣አደረጃጀት፣የሰው ሀይል አስተዳደር እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ምክረ ሀሳብ ያካተተ የጥናት ሰነድ አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

በዚሁ በቀረበው የጥናት ሰነድ ላይ የሚመለከታቸው የባለ ድርሻ አካላት በተገኙበት በተደረገ ውይይት የጥናት ሰነዱ የለያቸው ችግሮች በፍርድ ቤቱ በእርግጥም የሚታዩና መፍትሔ ሊበጅላቸው የሚገባ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በጥናቱ የተለዩትን ችግሮች ዘላቂነት ባለው መልኩ ሊፈቱ የሚችሉት የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 188/1992 ሲሻሻል መሆኑ ድምዳሜ ላይ መደረሱን ተከትሎ ክቡር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ቀደም ሲል ከነበሩት የኮሚቴ አባላት በተጨማሪ 2 ክቡራን ዳኞችን በኮሚቴነት በማካተት በድምሩ 7 የኮሚቴ አባላት በማዋቀር የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማሻሻያ አዋጅ ጥናት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ይህም ረቂቅ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ የፌደራል ፍርድ ቤት፣የፌደራል ፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አመራሮች፣ዳኞች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህግ ባለሙያዎች ባሉበት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ከዳበረ በኋላ ለፍትህ ሚኒስቴር፣ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲሁም ለፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ቀርቦ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በመገምገም አስተያየታውን የሰጡበት ሲሆን በተሰጡ አስተያየቶች መሰረትም ረቂቅ አዋጁን የማስተካከል ሥራ ተሰርቷል፡፡

# የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የተሻሻለ አዋጅ ረቂቅ ላይ ከቀድሞው አዋጅ የተሻሻሉና የተጨመሩ አንቀጾች የመሻሻላቸው፣ የመጨመራቸውና የአገላለጻቸው ሐተታ ዘ-ምክንያት

## መግቢያ

በመግቢያው ክፍል ውስጥ ከዚህ በፊት የተቋቋመና በአዋጅ የተቋቋመበት ምክንያት የሚታወቅ ፍርድ ቤትን የሚመለከት በመሆኑ የቀድሞውን አዋጅ መግቢያ ከመድገም ይልቅ የተሻሻለው ረቂቅ አዋጅ የሚወጣበት ምክንያት ላይ ብቻ በማተኮር የቀድሞውን አዋጅ መግቢያ በአጭሩ አስታውሶ ማለፍና የተሻሻለበትን ምክንያት መጥቀስ ብቻ በቂ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የረቂቅ አዋጁን ህገ መንግስታዊ መሰረት፣ አስፈላጊነት፣ የተቋሙን በህልውና መኖር ከመግለጽ ባሻገር ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት ሲገለጽ የተቋሙን አስተዳደር ለማጠናከር፣ የፍርድ ቤቱን ነጻነት ለማረጋገጥ፣ አደረጃጀቱን ለማሻሻልና ለዘላቂ እድገትና ልማቱ የሚያስፈልጉትን የዳኝነት አስተዳደር አካላት ለመገንባት መሆኑ መግለፅ አስፈላጊ በመሆኑ መግቢያው ይህንን በሚያስረዳ መልኩ ተለውጧል፡፡

በጠቅላላው ማሻሻያው ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች የፍርድ ቤቱን ነፃነት ይበልጥ ለማረጋገጥ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት አሠራር ለመዘርጋት እና በቅርቡ በሀገሪቱ የፍትህ ሥርዓት ውስጥ የተደረጉ የህግ ማዕቀፍ ለውጦችን ለማጣጣም እና የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቱም አንዱ የሪፎርም አካል መሆኑ መገለጽ አለበት፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ አንድ፡-

**የአዋጁን አጭር ርዕስ**፡ በሚመለከት ከዚህ በፊትም የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ የነበረና ተቋሙም አዲስ ሳይሆን ነባር ተቋም መሆኑን ለመጠቆም ያክል “የተሻሻለ” የሚል ቃል

ሊኖረው የሚችል ቢሆንም ይህ ቃል የቀድሞው አዋጅ ከዚህ የተሻሻለ አዋጅም በኋላ ተፈጻሚነት ያለው እንዳያስመስል ለማድረግና አዋጁንም በቀላሉ ለመጥራት አመቺ ለማድረግ ካስፈለገ በአጭሩ "የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ" ተብሎ ቁጥሩን ማስከተል ይቻላል፡፡

<u>**አንቀጽ ሁለት፡-**</u>

<u>**በትርጉም ክፍል ውስጥ**</u>፡ ከዚህ በፊት ከተካተቱ ቃላትና ሀረጎች በተጨማሪ **ቃዲና ዋና ቃዲ** የሚሉት ቃላት በ**"ዳኛ" እና "ፕሬዳዝንት"** የሚሉ ቃላት የአንድ ፌዴራል ፍርድ ቤት አካል እንደ መሆናቸው መጠን ተመሳሳይ መገለጫና ቋንቋዎችን ለመጠቀም እንዲያስችል ተቀይረዋል፡፡ ከዚህ ውጪ የተጨመሩት የትርጉም ቃላትና ሀረጎች ከተሻሻሉና ከተጨመሩ የአዋጁ ክፍሎች ጋር በተገናኘ የተጨመሩና አዋጁን ይበልጥ ለመረዳት ያስፈልጋሉ የተባሉ ቃላትና ሀረጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ ያላቸው ትርጉም የተገለጸበት ድንጋጌ ነው፡፡ በሰበር ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመለየት "መሠረታዊ የሸሪዓ ሕግ አተረጓጎም ስህተት" ለሚለው ሐረግ ዝርዝር ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

<u>**አንቀጽ ሶስት፡-**</u>

<u>**ተጠሪነትን በሚመለከት**</u>፡ሁለት አማራጮች ላይ ሰፊ ውይይት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በመጨረሻ የተመረጠው አማራጭ ፍርድ ቤቶቹ የፌዴራል ፍርድ ቤቶቹ አካል ሆነው መቀጠላቸው አስፈላጊነት ላይ አርቃቂው ኮሚቴ ተስማምቷል፡፡ በረቂቁ ውስጥ የተካተተው ሁለቱም አማራጮች ከታች በአዋጁ ውስጥ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ሊቋቋም ስለሚገባበት አመክንዮ የቀረበው የማሻሻያ ምክንያት ስር በዝርዝር ተጨባጭ ህገ መንግስታዊ መነሻ እንዳላቸው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

አንደኛው አማራጭ አሁን ያለውን የፍርድ ቤቶቹን የፌዴራል ፍርድ ቤት አካልነትን በማስጠበቅ ነገር ግን የራሳቸው አስተዳደር ጉባዔ በማቋቋም ጉባዔውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ማድረግ ነው፡፡

ይህንኑ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ግንኙነት በሚያጠናክር መልኩ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔው ሰብሳቢም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ እንዲሆኑ ማድረግ አግባብ ነው፡፡

ይህ አማራጭ ከዚህ በፊት ከነበረው የፍርድ ቤቱ ባለቤትነት ጥያቄን የራሱን ጉባዔ በማቋቋም ብቻ ሳይሆን በቀድሞው አዋጅ ውስጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር ተያይዞ የነበሩትን ኃላፊነቶች ለራሱ ለሸሪዓ ፍ/ቤቱ፣ ለፕሬዝዳንቱና ለአስተዳደር ጉባዔው በመስጠት የፍርድ ቤቱን የራሱን የማስተዳደር አቅም የሚያጎለብት ማሻሻያ ነው፡፡

ሁለተኛው አማራጭ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን በቀጥታ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በራሱ አስተዳደር ጉባዔ አማካኝነት ማድረግ ሲሆን ይህንን አማራጭ የተለያዩ ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ህገ መንግስታዊ መሰረቱን የሚተቹት በመሆኑ በዋነኛ አማራጭነት አልቀረበም፡፡

ሶስቱንም ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተናጠል ከማቋቋም ይልቅ የስልጣን ተዋረዳቸውን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ የፌዴራል መጀመሪያ እና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹን ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተጠሪ የማድረግ ተጨማሪ ማሻሻያም ተካቷል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የፍርድ ቤቶቹ የወል ዳኝነት ስልጣንና ፍቃደኝነት</u>

<u>አንቀጽ አራት</u>፡-

**<u>የወል ዳኝነት ስልጣንን</u>፡** በሚመለከት ምንም እንኳ እነዚህ ድንጋጌዎች በመርህ ደረጃ ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረጉ ናቸው ቢባልም አዋጁ የጉዳዮቹን ዓይነት ሲያስቀምጥ ምሳሌያዊ (illustrative) ዝርዝር ሳይሆን የተሟላ (exhaustive) ዝርዝር ተጠቅሞ መዝጋቱና ፈቃደኝነት መገለጽ ያለበት ክርክር በሚነሳበት ወቅት ብቻ ከመጥሪያ ጋር በሚደርስ ፍቃደኝነት ማሳወቂያ ቅጽ በመሙላት መሆን እንዳለበት በአንቀጽ 5(1) ስር መደንገጉ ፍርድ ቤቶቹ የወል ዳኝነት ስልጣን ከግልግል ዳኝነት ተቋም ስልጣን እንኳን ያጠበበና ለሥራ እንቅፋት ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

በሀገራችን በርካታ ሸሪዓውን መሰረት ያደረጉ ግንኙነቶች የሚከናወኑና እነዚህን ግንኙነቶች የሚጀምሩ ወገኖች ህገ መንግስቱ በጠበቀላቸው የእምነት ነጻነት መብት በመጠቀም በመካከላቸው ያሉ ጉዳዮችን ሸሪዓው መሰረት አድርገው እንዲመሰረቱና አለመግባባቶቻቸውም ሸሪዓውን መሰረት አድርገው እንዲዳኙ ሊስማሙ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቢያንስ

ሌሎች የግልግል ዳኝነት አካላት ያላቸውን ያክል በተከራካሪ ወገኖች ፍቃድ የመዳኘት ስልጣን ሸሪዓ ፍድ ቤቱ ሊኖረው የሚገባ በመሆኑ፤

ይህን መሰል ግንኙነቶች አሁንም መደበኛ ባለሆነ (informal) አሰራር በየመስጂዱና በየሀይማኖት አዋቂው ዘንድ ባለጉዳዮች ስምምነቶችን የሚያደርጉና አለመግባባቶን ለመፍታት የሚጥሩበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም ይህንን አማራጭ የግጭት አፈታት ስርዓት ህጋዊ በሆነው በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ጥበቃ ቢከናወን የተሻለ በመሆኑ፣

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ተከራካሪዎች በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ያላቸውን ፍቃደኝነት መግለጽ ያለባቸው ግንኙነቱ ሲጀመር ሳይሆን በክርክር ወቅት ብቻ መሆኑ የፍርድ ቤቶቹን የዳኝነት ስልጣን የሚያጠብ ሌላ ማነቆ በመሆኑ፣

ሌሎች በርካታ በፍርድ ቤቶቹ መገልገል የሚፈልጉ የማህበረሰባችን ክፍሎች መኖራቸውና የፍርድ ቤቱ ስልጣን ፍቃደኝነት ላይ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ይህን መሰል ስልጣኑን የሚያጠቡ ድንጋጌዎች ቀሪ ሆነው በምትካቸው ህገ መንግስታዊ መርሁን በጠበቀ መልኩ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ስልጣን መስፋት የሚችልና መስፋት ያለበት በመሆኑ፣

በጠቅላላው የአዋጁ አንቀጽ 4 እና 5 ስር የተቀመጡት የፍርድ ቤቱ የዳኝነት ስልጣን ድንጋጌዎች ህገ መንግስታዊ መርሁን በጠበቀ መልኩ እንኳን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር ሊወድቁ የሚችሉ ጉዳዮችን በእጅጉ ያጠበቡና የፍርድ ቤቱን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በእጅጉ የሚሸረሽሩ ናቸው፡፡

**<u>አንቀጽ አምስት</u>፡-**

**<u>የፍቃደኝነት አገላለጽን በሚመለከት</u>፡** የቀድሞው አዋጅ ፍቃደኝነት መግለጽ በሚል ያስቀመጠበት ሁኔታ በራሱ አሻሚና ፍርድ ቤቶቹን ለበርካታ ተግባራዊ እንቅፋቶች ያጋለጠ በመሆኑ ሊሻሻል ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም በሀይማኖቱ ሊቃውንት አስተያየት መሰረት አንድ ሰው በሸሪዓ ለመዳኘት ፍቃደኝነቱን ሰጥቷል የሚባለው የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ በመሆኑ ብቻ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም አልፎ አንድን ሙስሊም ነኝ ያለን ግለሰብ በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፍቃደኛ መሆን አለመሆኑን መጠየቅ ለዳኛው (ቃዲውም) በሀይማኖቱ የሚያስኮንን ከመሆኑም በላይ መሰረታዊ የሸሪዓ ህግ ጥሰት ያለበት አሰራር እንደሆነ ያምናሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የህግ ማዕቀፍ አሰራርና የተገልጋይ እርካታ ጥናት ግኝትም የሚያሳየው ለአንድ ሙስሊም አቅሙ በፈቀደው ልክ በሸሪዓ ህጉ አለመዳኘት ከእስልምና ሀይማኖት እቅፍ እንደመውጣት እንደሚቆጠር የቅዱስ ቁርዓን ምዕራፍ 5 አንቀጽ 44፣ 45፣ እና 47 ላይ የተደነገገውን መሰረት በማድረግ የቀድሞውን አዋጅ የፍርድ ቤቱን ዳኝነት ስልጣን በፍቃደኝነት ላይ መመስረት የሚተቹ በርካታ ባለሙያዎች አሉ፡፡

ይህ የሀገራችንን ህገ መንግስት የሀይማኖት ነጻነት መርህ ብቻ ሳይሆን የመንግስትና ሀይማኖት መለያየት እንዲሁም የዲሞክራሲያዊ መብቶች መርህን መሰረት አድርጎ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ደግሞ የሀገራችን ህገ መንግስት አንቀጽ 34(5) በግልጽ ለሀይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት የሚሰጠው ስልጣን የተገልጋዩን ፍቃድ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ይህንን ህገ መንግስታዊ መርህ የሚጥስ አዋጅ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ይህ የተሻሻለ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችም አዋጅ በመርህ ደረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን ፍቃደኝነት ላይ መሰረት አድርጎ የተቀረጸ ነው፡፡

ነገር ግን የቀድሞው አዋጅ ፍቃደኝነትን የመግለጽ ቅድመ ሁኔታን ማስቀመጡ ከላይ በዝርዝር እንደተቀመጠው በተዘዋዋሪ የፍርድ ቤቱን አቅም የሚያዳክም ብቻ ሳይሆን ለአሰራር የማያመች፣ ክርክሩ ከተጀመረም በኋላ በርካታ አጨቃጫቂ ሁኔታዎች የሚፈጥርና የሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች መብትና ጥቅም ያላገናዘበ በመሆኑ ሊሻሻል ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የፍቃደኛነትን መርህ የህገ-መንግስቱን መንፈስ በተከተለ እና የነበረዉን ችግር ሊያስተካክል በሚችል መልኩ ተሻሽሎ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተተኪ ተከራካሪዎችና የጣልቃ ገቦች የፍቃደኝነት ማረጋገጫ መንገዶች በቀድሞው አዋጅ ውስጥ ያልነበሩ በመሆኑ እልባት ሰጪ ድንጋጌዎች ተጨምረዋል፡፡ በክርክር ሂደት ውስጥ የሚገቡ ሦስተኛ ወገኖች ወይም ተተኪዎች ፈቃደኝነትን በተመለከተ ግልጽነት ለመፍጠር አዳዲስ ድንጋጌዎች ተጨምረዋል ፡፡

በተለይም ህገ መንግስታዊ መርሁ እንደተጠበቀ ሆኖ ግንኙነቶች በሚመሰረቱባቸው ሰነዶችና ውሎች እንዲሁም ክርክሩ ከተጀመረ በኋላ የፍርድ ቤቱ ዳኝነት ስልጣን ላይ ፍቃደኝነት ከተገኘ በኋላ የፍርድ ቤቱን ስልጣን መልሰው የሚነጥቁ አሰራሮችና የሌላኛውም ተከራካሪ ወገን መብትና ጥቅም ባገናዘበ መልኩ የተቀረጹና የተሻሻሉት ድንጋጌዎች በአዲሱ ረቂቅ አዋጅ ተካተዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የፍርድ ቤቶቹን የደረጃ ስልጣን

**የየደረጃው ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ስልጣን በሚመለከት**፡ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሶስት ደረጃ ተቋቁመው እውቅና እንደተሰጣቸው የቀድሞው አዋጅ እውቅና ቢሰጥም የነዚህ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ላይ በርካታ ክፍተቶች አሉበት፡፡ በየደረጃው የተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች ማለትም የመጀመሪያ፣ ከፍተኛና ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በገንዘብ መጠንና በጉዳይ አይነት በግልጽ ተለይቶና ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ አለመቀረጹ፣በተለይም በጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ቋሚ የሰበር ሰሚ ችሎት አለመኖር፣ የከፍተኛ እና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የየራሳቸው የህግ ሰውነትና አስተዳደር አለመኖር፣የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚያያቸው በገንዘብ የሚተመኑ ጉዳዮች የግምት ጣሪያ አነስተኛ መሆን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በርግጥ በአሁኑ ወቅት የየደረጃው ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የጉዳይ ፍሰትና ዓይነት ውስን ከመሆኑ አንጻር የነዚህን አንቀጾች መሻሻል የግድ አይደለም፡፡ ነገር ግን የሀገራችን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተገቢው ተደራሽነት ሲኖራቸውና መኖራቸውን እንኳን የማያውቀው ሰፊው የሙስሊሙ ማህበረሰብ ክፍል በፍርድ ቤቱ መጠቀም ሲጀምር እንዲሁም ከዚህ ከአዋጁ መሻሻል ጋር ተያይዞ ሊመለከቷቸው ከሚችሏቸው ተጨማሪ ጉዳዮች አንጻር የየደረጃው ፍርድ ቤቶች መስፋፋትና መጠናከር የግድ ይላል፡፡

**አንቀጽ ስድስት፡-**

**የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱን በሚመለከት**፡ በፌዴራሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች መካከል መሰረታዊ የሆኑ የትርጉም ልዩነት ያለባቸው የሸሪዓውን ህግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲነሱ ብቻ ባለ አምስት ዳኞች ጉባዔ የመሰየም ስልጣን ለዋና ዳኛ ተሰጥቶታል እንጂ ቋሚ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት የሌለ መሆኑ፣

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተደራሽነትን በከፍተኛ ሁኔታ ከመቀነሱ በላይ የክልልና የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን የሚያገናኛቸው ምንም ዓይነት ህጋዊ መሰረት እንዳይኖር እንዲሁም የውሳኔዎች ወጥነትና ተገማችነት እንዳይኖር አድርጎታል፡፡ ከዚህ አንጻር የቀድሞው አዋጅ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቱ የሰጠውን መሰረታዊ የሸሪዓ ህግ አተረጓጎም ስህተት የሚያይ ባለ አምስት ዳኛ

ጊዜያዊ ችሎት ወደ ቋሚ ሰበር ችሎትን የሚቀይር ንዑስ አንቀጽ ተጨምሯል፡፡ ነገር ግን ይህ ቋሚ የሸሪዓ ሰበር ሰሚ ችሎት አዋጁ እንደወጣ ሳይሆን በፍርድ ቤቶቹ የሚጠበቀው ለውጥና የመዝገብ ፍሰት ሲጨምርና በቂ በጀትም ሲኖር እንደሚሆን መደንገጉ አስፈላጊ በመሆኑ ይህም በረቂቅ አዋጁ ተካቷል፡፡ ቀደም ሲል የነበረው ጊዜያዊ ሰበር መሰል አሠራር ለሕግ ትርጉም ወጥነትና ተገማችነት በቂ ባለመሆኑ፣ ቋሚ ችሎት መኖሩ በሀገር ደረጃ ወጥ የሆነ የሸሪዓ ሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ያስችላል፡፡

<u>አንቀጽ ሰባት</u>፡-

**<u>የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ስልጣንን በሚመለከት</u>**፡ በቀድሞው አዋጅ ውስጥ የነበሩ ድንጋጌዎች ላይ መሰረታዊ ለውጥ የማያስፈልግ ቢሆንም ለከፍተኛው ሸሪዓ ፍርድ ቤት መለየት ያለባቸው ስልጣኖች ተለይተው የተቀመጡበት ድንጋጌ ተካቷል፡፡ በተለይም በአዲስ መልኩ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ይመለከቱታል ተብሎ ከሚገመተው የገንዘብ ግምት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ከፍተኛው ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚመለታቸው አነስተኛ የገንዘብ መጠን ከፍ መደረጉን የሚያሳዩ ድንጋጌዎች ተጨምረዋል፡፡ ይህም ፍርድ ቤቶቹ ለወደፊቱ ይመለከቷቸዋል ተብሎ ከሚገመተው ጉዳይ ብዛትና ስብጥር አንጻር እንዲሁም ይመለመላሉ ተብሎ ከሚጠበቁ ተጨማሪ የትምህርትና ስራ ልምድ ያላቸው ዳኞች አንጻር የተሻለ ሙያዊ ዝግጅት ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት የሰጠ ማሻሻያ ነው፡፡

<u>አንቀጽ ስምንት</u>፡-

**<u>የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ስልጣን በሚመለከት</u>**፡ ከቀድሞው አዋጅ የተለየ ምንም ዓይነት ድንጋጌ ያልተጨመረ ሲሆን ከከፍተኛው ሸሪዓ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የተደረጉ ጉዳዮችና ግምታቸው ከብር 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) ብር በታች የሆኑ ጉዳዮችን በሙሉ የማየት ስልጣን የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ስልጣን እንዲሆን የተደረገ ማሻሻያ ብቻ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሰራር</u>

በፍርድ ቤቶቹ ላይ በተከናወነው የጥናት ግኝቶች መሰረት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 ሊሻሻሉ ይገባል ተብሎ ከተጠቆሙ ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው የፍርድ ቤቶቹ አደረጃጀት ነው፡፡

የነዚህ ድንጋጌዎች መሻሻል ፍርድ ቤቶቹን ተደራሽ ለማድረግ፣ አገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማሻሻልና የተገልጋይ እርካታን ለማሳደግ አንዱና ዋነኛው መንገድ የፍርድ ቤቶቹን አደረጃጀት ማሻሻልና ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የህግ ማዕቀፎችን ከወዲሁ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የበታች የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተጠሪነት ግን ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሆኗል፡፡ ይህም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን የውስጥ የሥራ ተዋረድ ግልጽ ያደርገዋል፡፡በተለይም፡-

ምድብ ችሎቶችን ከማስፋፋት አንጻር የፌደራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ የተቋቋሙት የመጀመሪያና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎቶችን መጨመር ቢያስፈልግ ምድብ ችሎቶቹ የሚቋቋሙባቸውን አካባቢያዊ ስብጥርና የሚያስፈልጉትን ችሎቶች የመወሰን ስልጣን በግልጽ ለማንም ያልተሰጠ በመሆኑ አዋጁ አንቀጽ 9፣ 10 እና 11 ላይ መጠነኛ ማሻሻያዎችን በማድረግ የፍርድ ቤቱን የወደፊት እድገት ማረጋገጥ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

<u>አንቀጽ ዘጠኝ፡-</u>

<u>**የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱን አደረጃጀት በሚመለከት**</u>፡ ከቀድሞው አዋጅ እምብዛም ለውጥ ባያስፈልግም ዋና ቃዲ የሚለው ሀረግ በፕሬዝዳንት የተቀየረ ሲሆን ይኸውም ከላይ እንደተገለጸው ለተመሳሳይ የፍርድ ቤት ቋንቋ አጠቃቀም የሚረዳና አሁንም በተግባር ላይ የሚገኘው አገላለጽ በመሆኑ ነው፡፡

<u>አንቀጽ አስር፡-</u>

<u>**የፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አደረጃጀት በሚመለከት**</u>፡ በዚህ አንቀጽ ስር ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችም ፕሬዝዳትና ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሁም ተጨማሪ ለሚቋቋሙ ምድብ ችሎቶች ተጠሪ ዳኛ እንደሚኖር ተጨማሪ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

<u>አንቀጽ አስራ አንድ</u>፡-

<u>**የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማስቻያ ስፍራን በሚመለከት**</u>፡ መሻሻል ያለበት ዋነኛ ጉዳይ የምድብ ችሎቶች ብዛት መጨመር አስፈላጊነትን፣ የምድብ ችሎቶች ብዛትና አመሰራረት ለተገልጋዩ ማህበረሰብ ተደራሽ መሆኑን ባረጋገጠ መልክ መደረግ ያለበት መሆኑን በሚጠቁም

መልኩ ሲሆን ይህንንም በአዋጁ አንቀጽ 13 ስር አንድ ንዑስ አንቀጽ በመጨመር ማሳካት ይቻላል፡፡ ከቀድሞው አዋጅ ድንጋጌዎች በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት አያስፈልጉም ቢባል እንኳ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ እውቅናቸው ጨምሮ በሙሉ አቅማቸው መስራት በሚጀምሩበት ወቅት የሚያስፈልገውን ምድብ ችሎቶች ለማብዛት የሚስያችል የህግ ፍቃድ የሚሰጥ ድንጋጌ ተጨምሯል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ምድብ ችሎቶች ለመጀመሪያ እና ለከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ቢያስፈልጋቸው የማደራጀት ስልጣን ለማን እንደተሰጠ አሁን በሥራ ላይ ያለው አዋጅ በግልጽ የማያስቀመጥ የነበረ በመሆኑ በዚህ አዋጅ ሌሎች ክፍሎች ውስጥ ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንት ስልጣንና ኃላፊነቶች መካከል እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ አስራ ሁለት</u>፡-

<u>**ከፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የስራ ቋንቋ ጋር ተያይዞ**</u>፡ የተደረገ ምንም ዓይነት መሰረታዊ ለውጥ የለም፡፡ የፌዴራል ተቋም እንደመሆኑ መጠን ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ሊኖረው የሚችለው የሥራ ቋንቋ አይነትና ብዛት በፌዴራል መንግስቱ የሚወሰኑትን እንደሆነ መጥቀስ በቂ ነው፡፡

<u>አንቀጽ አስራ ሶስት</u>፡-

<u>**በግልጽ ችሎት ስለማስቻልና ከችሎት ስለመነሳት**</u>፡ የተቀመጡት ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 188/1992 እንደሌሎች በርካታ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የሸሪዓ ህጉን ከግምት ውስጥ ያስገቡ አይደሉም፡፡ ከዚህ አንጻር ይህንን ድንጋጌ በማሻሻል በግልጽ ችሎት ማስቻልንም ሆነ ከዳኝነት መነሳትን በሚመለከት ከፍ/ብ/ሥ/ሕጉ በተጨማሪ የሸሪዓ ህጉን መርሆች እንዲሁም ለወደፊቱ ከታቀደው ሸሪዓ ህግ ማጣቀሻ መድብሎች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተርጎም እንደሚገባው የሚደነግጉ አገላለጾች ተካተዋል፡፡

<u>አንቀጽ አስራ አራት</u>፡-

<u>**ለዳኛነት ከሚያበቁ መስፈርቶች**</u>፡ ጋር በተያያዘ የቀድሞው አዋጅ ውስጥ የግልጽነት ጥያቄ ሊያስነሱ የሚችሉት "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ" የሚለው ሀረግና ስለሸሪዓ ህግ ትምህርት ዝግጅት የተቀመጡት አማራጮች ተቀምጠዋል፡፡

የሸሪዓ ህግ ትምህርት ዝግጅት መስፈርት ያለ ሌላ ስራ ልምድም ሆነ ተጨማሪ መመዘኛ ለመጀመሪያ ደረጃ፣ ለከፍተኛም ሆነ ለጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተፈጻሚነት ያለው መሆኑም

ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ወደ ላይ ላሉት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ደረጃዎች ተጨማሪ የስራ ልምድ መስፈርት ሆኖ አልተቀመጠም፡፡

በርግጥ ከከፍተኛ የሸሪዓ ህግ ትምህርት ተቋማት የሸሪዓ ህግ ትምህርት ማጠናቀቅ ማረጋገጫ ዲግሪ እንደ ዋነኛ መስፈርት እንዲቀመጥ የተሰጡ አስተያየቶች ነበሩ፡፡ ነገር ግን በሀገራችን በአሁኑ ሰዓት አንድም በአቻ ምዘና ደረጃ እንደ እስልምና ሀይማኖታዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋምነት የተመዘገበም ሆነ በስራ ላይ የሚገኝ ተቋም ባለመኖሩ ይህ ማሻሻያ ቢካተትም እንኳን ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ በተጨማሪም በሀገራችን የታወቁና ለበርካታ ክፍለ ዘመናት የሸሪዓ ህግ ትምህርት በባህላዊ መንገድ ከሚሰጥባቸው ተቋማትና ከሚሰጡ ታላላቅ ሊቃውንት ዘንድ በመማር ከፍተኛ ሸሪዓ ህግ እውቀት ያካበቱ ዳኞችንም ሊያሳጣ የሚል በመሆኑ እንደ መሰረታዊ መስፈርትነት ሊካተት አይገባውም የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

የዳኞች ምልመላና አመራረጥ ስራ ላይ የቀድሞው አዋጅ ዝርዝር ያስቀመጠው ነገር ባለመኖሩና የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ አስተዋጽዖ በአዋጁ ውስጥ አልተካተተም፡፡ ከዚህም በላይ ግልጽና የተብራራ የምልመላና መረጣ አሰራርና መመሪያ የሌለ ከመሆኑም በላይ ይህንንም መመሪያ የማዘጋጀት ስልጣንና ኃላፊነት እንኳ ለማንም አልተሰጠም፡፡ ስለዚህ የአዋጁ አንቀጽ 14 ተሻሽሎ እነዚህ ተጨማሪ መስፈርቶችን ባካተተና ዝርዝር መመሪያ እንደሚወጣና የሚያወጣውን አካል የሚለይ አቀራረጽ አካቶ ሊረቀቅ ይገባዋል፡፡

በተለይም ይህ አዋጅ ተሻሽሎ ከዚህ በኋላ ለምን ያክል ዓመታት እንደሚያገለግል ማወቅ የማይቻል በመሆኑና የአቻ ምዘና መስፈርትን የሚያሟሉ እስላማዊ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለወደፊቱ እንደሚቋቋሙ ጠቋሚ እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡ ከዚህም በላይ በአሁኑ ሰዓት በውጪ ሀገር የሸሪዓ ትምህርታቸውን አጠናቀው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሰርተፍኬቶችና ዲግሪዎች የያዙ የሸሪዓ ህግ ባለሙያዎችም እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ነባራዊ ሁኔታዎች በሚያስታርቅና ፍርድ ቤቱን የሰለጠኑ ባለሙያዎች እንዳያጣ በሚደርግ መልኩ እነዚህ ድንጋጌዎችን ማሻሻል ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ተጨማሪና ዝርዝር የዳኛነት ምልመላና አመራረጥ መመሪያ እንደሚወጣ የሚደነግጉ አንቀጾች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ አስራ አምስት</u>፡-

<u>የዳኞች አሿሿም</u>፡ በሚለው ድንጋጌ ውስጥ የተካተቱና ሊካተቱ ይገባቸዋል ተብለው የሚታመኑ ህግጋቶች ከፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ተጠሪነት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡

ስለዚህ ዝርዝር ምክንያቱ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔው ማቋቋሚያ የአዋጁ አንቀጾች ማሻሻያ ስር መመልከት የሚቻል ሲሆን በዚህ አንቀጽ ስር የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት አሿሿምን በሚመለከት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት እንዲሆን የሚለው ላይ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎችም ሆነ ከጥናቱ ግኝት አንጻር የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን በአዋጅ ባቋቋመው አካል መከናወኑ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሌሎች ሸሪዓ ፍርድ ቤቱን ዳኞች አሿሿም በሚመለከት ደግሞ ሁለት ዓይነት የዳኞች አሿሿም ስርዓት አማራጮች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

የመጀመሪያው አማራጭ የነበረው ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አሿሿም ሂደትን ቀልጣፋ ለማድረግና ከዚህ በፊት የነበረውን የዳኞች ሹመት ጥያቄ መዘግየት እልባት በሚሰጥ መልኩ በፌ/ጠ/ሸ/ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በፌ/ሸ/ፍ/ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ፊት እንዲጸድቅ የማድረግ ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ለዳኞች የበርካታ አመታት የእኩልነትና የዳኝነት ነጻነት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚቻለው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት እንደሌሎች የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት እንዲሆን ሲደረግ ብቻ ነው የሚል አማራጭ ነው፡፡

በመሆኑም ከፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት ውጪ ያሉ ዳኞችና ፕሬዝዳንቶችም በሙሉ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት ሹመታቸው እንዲጸድቅና አቅራቢን በሚመለከት ግን የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳት አንድ ጊዜ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት ሹመቱ እስከተረጋገጠ ድረስ የተቀሩትን የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት አቅርቦ የማስጸደቅ ስልጣንም ቢሰጠው የዳኛነት ሹመት ሂደቱን ለማቀላጠፍ ይረዳል የሚረዳ በመሆኑ በዚሁ መልኩ ተሻሽሏል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ ጋር በተያያዘ ሹመት የመጽደቅ ጉዳይ በየትኛውም ተቋም ፊት ሆነ በየትኛውም አመራር አቅራቢነት የሚከናወነው የዳኞች መብትና ጥቅም ላይ ተጽዕኖ እንዳይኖረው ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ከቀረቡት አማራጮች በተጨማሪ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በዋነኝነት የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ትይዩ የፍትህ አካላት ዳኞች በመሆናቸው ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ጋር ተመሳሳይ መብት፣ ጥቅምና ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ድንጋጌ መኖር ያለበት በመሆኑ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ድንጋጌ ተካቷል፡፡

አንቀጽ አስራ ስድስት፡-

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን በጀት በሚመለከት፡ በቀድሞው አዋጅ ስለ በጀት በአንቀጽ 19 ስር የተቀመጠው ላይ ለውጥ ባያስፈልግም ይህንን በጀት የማፈላለግና ማስፈቀድ ኃላፊነት እንዲሁም ሪፖርት የሚደረግበትን ስርዓት በሌሎች ድንጋጌዎች ስር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ፕሬዝዳንቶች፣ ምክትል ፕሬዝዳንትና ተጠሪ ዳኞች

ከላይ እንደተገለጸው የቀድሞ አዋጅ አንቀጽ 3 የሚያቋቁመው ሶስት ደረጃ ያለው ፍርድ ቤት ቢሆንም ለሶስቱም ደረጃ ፍርድ ቤቶች ግልጽ ለእያንዳንዱ ደረጃ ፍርድ ቤት የራሱ የህግ ሰውነት እንዳለው የሚያሳይ አደረጃጀትን ግን አያስቀምጥም፡፡ ከዚህ አንጻር የቀድሞው አዋጅ ይህንን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በማሻሻል የራሳቸው አመራር አካላት እንዲኖሯቸው ማድረግና ለአመራሮቻቸውም አስፈላጊውን ስልጣንና ኃላፊነት በተገቢው የአዋጁ ክፍሎች ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል፡፡

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶችና ተጠሪ ዳኞች ስልጣንና ኃላፊነት ከመደንገጉ በፊት በማንና እንዴት እንደሚሾሙ እንዲሁም ለወደፊቱም ሌሎች አስፈላጊ አመራር አካላትን መሾም እንደሚቻልና በማን መሾም እንደሚችሉና መቼና እንዴት ከኃላፊነታቸው ሊነሱ እንደሚችሉ የሚገልጹ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን የያዘ አንድ ተጨማሪ አንቀጽ ያስፈልጋል፡፡

በመቀጠል የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶችና ተጠሪ ዳኞችን በሚመለከት ከዚህ በማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ ውስጥ የፍርድ ቤቱን አስተዳደራዊ ነጻነትና አቅም ለማስተካከል ከቀረቡት መሻሻያ ሃሳቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ ሊታይ ይገባዋል፡፡

አንቀጽ አስራ ሰባት፡-

ጠቅላላ ድንጋጌዎች፡ የሚስፈልጉት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የህግ ማዕቀፎች ለማሟላት እንደመሆኑ ይህንን ዓላማ የሚያሳኩ ተጨማሪ ድንጋጌዎች በማካተት የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የሚመለመልበትና የሚሾምበት እንዲሁም የሚሻርበት ድንጋጌ፣ የመጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳቶች የሚመለመሉበትና የሚሾሙበት እንዲሁም ተጠሪ ዳኞች የሚሾሙበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

አንቀጽ አስራ ስምንት፡-

**የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባራትን**፡ የየደረጃው ፍርድ ቤት የራሱ የሆነ የህግ ሰውነት ያልነበረውና ይህም ለፍርድ ቤቱ እድገትና ጥንካሬ በባለቤትነት ተጠያቂ የሆነ አካል አልነበረውም፡፡ የዚህ አንዱና ዋነኛው መገለጫ የእያንዳንዱ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የሌለውና የራሱን አስተዳደርና ፋይናንስ እንዲመራ ስልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ፣

የፍርድ ቤቱን የድጋፍ ሰራተኞችንም ቢሆን የሚቀጥሩት በየትኛውም ጊዜ በቅድሚያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ፕሬዝዳንት ፍቃድ ጠይቀው ሲያገኙ ብቻ መሆኑ፣ ከድንጋጌው ግልጽነት አንጻርም ቢሆን ሰራተኛ "እንዲቀጠርለት ይጠይቃል" ካለ በኂላ መልሶ ሲፈቀድለት "ይቀጥራል" ማለቱ በርግጥም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን የድጋፍ ሰራተኞች የሚቀጥረው ማን እንደሆነ ለመለየት አዳጋች ያደረገው መሆኑ፣ ይህ "የማስቀጠር" ወይም "የማስፈቀድ" ግዴታም አዲስ ቅጥር ለመፈጸም ብቻ ይሁን የተጓደሉ ሰራተኞች ለማሟላት የሚደረግ የሰራተኛ ቅጥርን እንደሚያጠቃልል አዋጁ ግልጽ አለማድረጉ፣

እነዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤት አመራሮች የየደረጃቸውን ፍርድ ቤቶች እቅድና በጀት አዘጋጅተው ከማስፈቀድ በተጨማሪ የየፍርድ ቤቶቻቸውን ፋይናንስ የማስተዳደር ስልጣን በአዋጁ አለመስጠቱ፣

እንዲሁም ሌሎች በሰብሳቢ ዳኝነት የመሰየም፣ የዳኞች የስልጠና፣ ጥቅማጥቅምና ደረጃ የማስከበር ኃላፊነቶች፣ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ተግባር ላይ የማዋልና በተለይም የሸሪዓ ህጉን መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ የውስጥ መመሪያና ማኑዋሎችን የማዘጋጀት ስልጣንና ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑ በርግጥም ፕሬዝዳንቶቹ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ የበላይ አስተዳዳሪ ናቸው ለማለት ያዳግታል፡፡

ስለዚህ በዚህ ረገድ ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ብቻ ሳይሆን በየደረጃው ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለሚገኙ ፕሬዝዳንቶች እነዚህን ክፍተቶች የሚሞሉ ስልጣንና ተግባራት የሚሰጡ ድንጋጌዎች ተካተው አንቀጾቹ ተሻሽለው፤

የሶስቱም ደረጃ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች ተጨማሪ የሀብት ማሰባሰብና ማስተዳደር፣ የሰው ሀብት አስተዳደርና የፋይናንስ አስተዳደር ስልጣንና ኃላፊነትን ጨምሮ ሌሎችም አስፈላጊ ተግባራትን እንዲፈጽሙ በሚያችል መልኩ፣

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የተቋሙን አዳዲስ የአስተዳደር ሰራተኞች በራሱ ለመቅጠርና የተጓደሉ ሰራተኞችን ለመተካት ግልጽ ስልጣን መስጠትና የሸሪዓ ህጉን ያገናዘበ ተጨማሪ የአለባበስና የስነ ምግባር መስፈርትን ማስቀመጥ በሚያስችላቸው መልኩ ድንጋጌዎቹ ተሻሽለዋል፡፡

<u>አንቀጽ አስራ ዘጠኝ</u>፡-

<u>**የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባራትን**</u>፡ በሚመለከት ከቀድሞው አዋጅ የተለየ ድንጋጌ ባይካተትም በሌሎች ድንጋጌዎች ምክትል ፕሬዝዳንቱ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ አባል ሆኖ እንደሚያገለግል ተደንግጓል፡፡

<u>አንቀጽ ሀያ</u>፡-

<u>**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባራትን በሚመለከት**</u>፡- ከዚህ በላይ በተዘረዘረው አመክንዮ ተጠሪነታቸው ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ሆኖ የየፍርድ ቤቶቻቸው ባለ ሙሉ ስልጣን አስተዳዳሪ እንዲሆኑ የሚደነግጉ ከላይ ዝርዝራቸው የተቀመጡ ስልንጣንና ኃላፊነቶች ተስጥቷቸዋል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ</u>

ለዚህ ረቂቅ የተሻሻለ አዋጅ መነሻ የሆነው ጥናት እንደሚያሳየው ለፌዴራል ሸሪዓ ከፍርድ ቤቶች መዳከምና ለህልውናቸው አደጋ ላይ መውደቅ ዋነኛው ምክንያት የፍርድ ቤቶቹ አስተዳደርና ተጠሪነት ጉዳይ በቀድሞው አዋጅ ድንጋጌዎች በተለያዩ ቦታዎች ተሰባጥረው ለተለያዩ አካላት ተመድበው መኖራቸው ነው፡፡

አዋጁ በአንድ በኩል ፍርድ ቤቶቹ ተጠሪነታቸው፣የፍርድ ቤቱ ዳኞች ሹመት የሚከናወነውም ሆነ የዳኞችን የዲሲፕሊን ጥፋት መርምሮ የሚወሰነው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች

አስተዳደር ጉባዔ እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 3፣17(3) እና 18 እንደቅደም ተከተላቸው ይደነግጋሉ፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ የበላይ አመራሮች የሆኑት ዋና ዳኛ፣ ምክትል ዋና ዳኛና ተጠሪ ዳኞች መሆናቸው ደንግጎ ውስን የአስተዳደር ስልጣኖችን ይሰጣቸዋል፡፡

አዋጁ መልሶ ዋና ዳኛው በተጠሪነታቸውም ሆነ በሰራተኛ ቅጥራቸው፣ በበጀትና ሌሎች ጥያቄዎቻቸው፣በስራ አፈጻጸም ሪፖርትና አቀራረባቸውና የዳኝነት ምልመላ ጥያቄዎቻቸው በሙሉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ስር እንደሆኑ ይደነግጋል፡፡

ከዚህ እንደምንረዳው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የመደበኛው ፌዴራል ፍርድ ቤት እይታ ስር ያሉ ነገር ግን እራሳቸው የቻሉ ፍርድ ቤቶች እንዲሆኑ ታስቦ የተቀረጸ ህግ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ፍርድ ቤቶቹን ያለ ወሳኝ አካል ያስቀራቸው ነው፡፡

ከዚህ በፊት ስለ ፍርድ ቤቱ እድገትና ህልውና የሚጨነቅለት የተገልጋዩን ማህበረሰብ ክፍል ፍላጎትና ስሜት የሚያንጸባርቀው ብቸኛ አካል የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ነው፡፡ ይህ ተቋም ደግሞ የዳኝነት አስተዳደሩ አካል ባለመሆኑ ጣልቃ ገብነቱ ሊያስከትል የሚችለውን የዳኝነት ነጻነት መሸርሸር አስግቶት ፍርድ ቤቱ ህልውናው አደጋ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ምንም ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ አልቻለም፡፡

ስለዚህ ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው የፍርድ ቤቶቹ መስፋፋት፣ተደራሽነትና ዘላቂ ህልውና የሚሰራ የፍርድ ቤቶቹ አስተዳደር እጦት አጣብቂኝ ብቸኛው እልባት በቀድሞው አዋጅ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተሰጣቸውን በሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ላይ የመወሰን ስልጣኖች የፍርድ ቤቶቹን ነጻነትና ተጠያቂነት ባረጋገጠ መልኩ የሚያስተዳድር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የራሳቸው የአስተዳደር ተቋም በአዋጅ ማቋቋም ነው፡፡

ይህ ጉባዔ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ የሚለየው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞችን ጉዳይ ብቻ የሚመለከት አለመሆኑ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችም በተደጋጋሚ ባከናወናቸው የ "Judicial Administration" ማሻሻያ ጥናቶች ለተሻለ የዳኝነት አገልግሎት፣ ነጻነትና ለፍርድ ቤቶች ሁለንተናዊ ደህንነት የሚሻለው "የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ" ሳይሆን "የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ" ማቋቋም የተሻለ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ በዚህም ምክንያት

ነው የቀድሞው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 1233 በሚሻሻልበት ጊዜ የጉባዔው ስያሜ "የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ" በሚል የተቀየረው፡፡

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የዳኝነት አስተዳደር እድገትና ማሻሻያ መርህ በመከተልና አንድ ደረጃም በማሻገር በዳኞች ላይ ብቻ ሳይሆን በፍርድ ቤቱም ሁለንተናዊ እድገትና የአገልግሎት አሰጣጥ መጎልበት የሚሰራ ጉባዔ ለማቋቋም በማሰብ ይህ አዲስ የአዋጅ ክፍል በቀድሞው አዋጅ ላይ ተጨምሯል፡፡ ጉባዔውን በሚመለከት የተቀረጹት አንቀጾች በዳኝነት ስራና በዳኝነት ነጻነት ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ሳያስከትል የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለማስተዋወቅ፣ ለማስፋፋት፣ ለማጠናከርና በጠቅላላው የተገልጋይ እርካታን የሚያስገኝ ፍትህ ተቋም ለማድረግ ብቻ የሚሰራ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የሚመራ ጉባዔ ሆኖ እንዲቋቋም ነው የተደረገው፡፡

የዚህ ጉባዔን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹን ተጠሪነት በሚመለከት ከተለያዩ ባለሙያዎች የሚቀርቡ ሁለት ዓይነት ሃሳቦች አሉ፡፡

አንደኛው ሀሳብ "ከህገ መንግስታችን አንቀጽ 78(5) የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እራሳቸውን ችለው ከመቋቋም አያግዳቸውም የሚል ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 11 እና 27 አንጻር ሲታይ ከመንግስትና ሀይማኖት መነጣጠል መርህን በጠበቀ መልኩ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶቹ ተለይቶ በአዋጅ ሊቋቋሙ እንጂ የግድ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶቹ ጋር ተጣምረው እንደሆነ አይደነግግም፡፡ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 78(5) ዓላማ ተጠሪነቱ ለኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤትና ለየክልል ምክር ቤቶቻቸው ተጠሪ የሆኑ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም ወይም ያሉትን እውቅና ለመስጠት ነው፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችና የፍርድ ቤቶቹ አስተዳደር ጉባዔ ተጠሪነታቸው ፍርድ ቤቶቹን እንዲያቋቁማቸው በህገ መንግስቱ ስልጣን ለተሰጠው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሆኖ በጀትና ሪፖርታቸውም በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት አማካኝነት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀጥታ እንዲቀርብ ማድረግ ይቻላል፡፡" የሚል ሀሳብ ነው፡፡

ሁለተኛው ሀሳብ ደግሞ ከዚህ በላይ ከቀረበው አመክንዮ ተነጻጻሪ በሆነ መልኩ፤ "በሀገራችን ህገ መንግስት በፌዴራልና የክልል መንግስታዊ መዋቅር ውስጥ አንድ ህግ አውጪ፣ አንድ ህግ አስፈጻሚና አንድ ህግ ተርጓሚ አካል ብቻ እንደሚኖር በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50(2) ድንጋጌ የሚጠቁም በመሆኑ፣ በተጨማሪም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ የሚያዘውም አንቀጽ

78(5) የሚገኝበት የህገ መንግስታችን ምዕራፍ ዘጠኝ ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀር የሚደነግገው የህገ መንግስቱ ክፍል ውስጥ የሚገኝና ጥቅል ንባቡም የፍትህ ስርዓቱን የመጨረሻ የስልጣን እርከኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የሆነ አንድ የህግ ተርጓሚ አካል ብቻ እንደሚያቋምም የሚጠቁም በመሆኑና የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 78(4) የዳኝነት ስልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶችና በህግ የተደነገገውን ዳኝነት ስርዓት የማይከተሉ ልዩ ፍርድ ቤቶች ሊቋቋሙ እንደማይችሉ የተደነገገ ከመሆኑ አንጻር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ የሀገሪቱ የህግ ተርጓሚና የዳኝነት አስተዳደር አካል እንዲሆኑ መደረጋቸው ህገ መንግስታዊ መሰረታቸው ላይ ጥያቄ እንዳያስነሳ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ውስጥ ነው ሊቋቋሙ የሚችሉት" የሚል ሀሳብ ነው፡፡

ስለዚህ የፍርድ ቤቶቹ አስተዳደራዊ ነጻነት ሳይገፈፍ ከላይ በቀረበው አመክንዮ መሰረት የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ተቋቁሞ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ የሀገሪቱ የዳኝነት አስተዳደር አካል ይሆኑ ዘንድ ደግሞ ፍርድ ቤቶቹና ጉባዔው ተጠሪነታቸው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር እንዲሁም የበጀት ጥያቄያቸውንና ዓመታዊ የስራ ሪፖርታቸውን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት አማካኝነት ከፌዴራሉ ፍርድ ቤትና የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ በጀትና ሪፖርት ጋር የሚቀርብ እንዲሆን በማድረግ አዋጁ ቢሻሻል ሊያስነሳ የሚችለው የህገ መንግስታዊነትም ጥያቄ ሊኖር አይችልም፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቶቹ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ጋር ያላቸውን ቁርኝትና ተጠሪነት የጉባዔውን ፕሬዝዳንት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ፕሬዝዳት እንዲሆን በማድረግ ማጠናከር ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ አስተዳደር ጉባዔ ስልጣንና ተግባር በግልጽ ተቀምጦ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ላይ ባለሙሉ ወሳኝነት ስልጣን በዝርዝር መስጠት የፍርድ ቤቶችን ተጠሪነትና ሪፖርቲንግ ወጥ ለማድረግ የበጀት ጥያቄና ሪፖርታቸውን ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶችና የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በጀትና ሪፖርት ጋር በጋራ እንዲቀርብ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመቅረቡ ከአንድ ወር በፊት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅርበው እንደ አንድ የህግ ተርጓሚ አካል በጀትና ሪፖርት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ እንዲቀርብ በሚያስችል መልኩ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

**አንቀጽ ሃያ አንድ፡-**

**የጉባዔው መቋቋምን አስመልክቶ**፡ ከላይ በቀረቡት ሁለቱም ሃሳቦች የትኛውም ተፈጻሚ ቢሆን የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም አስፈላጊነት ላይ ከየትኛውም ባለድርሻ አካል የቀረበ ማስተባበያም ሆነ የተሻለ አማራጭ የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ጉባዔውን ለማቋቋም ሌላ አዋጅ ሳያስፈልግ በዚሁ አዋጅ ጉባዔውን ማቋቋም፣ አደረጃጀቱን፣ ስልጣንና ኃላፊነቱን፣ የበጀት ምንጩንና አሰራሩን መወሰን አልያም የሚወሰንበትን መመሪያና ደንብ የማውጣት ስልጣን መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**አንቀጽ ሃያ ሁለት፡-**

**የጉባዔውን አደረጃጀት በሚመለከት**፡ በርካታ ሀሳቦች የተነሱ ሲሆን የመጀመሪያው ተግባር በአዋጅ ቁጥር 1233 ስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባዔን በሚመለከት የተደነገጉትን በሞዴልነት መጠቀም ነበር፡፡ ነገር ግን ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የታሰበው ጉባዔ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ በዓላማ፣ በተግባርም ሆነ በስልጣንና ኃላፊነት የተለየ በመሆኑ የዳኞችም ሆነ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ሳይሆን የፍርድ ቤቶቹ አስተዳደር ጉባዔ እንዲሆን ነው የተመረጠው፡፡ የአባላቱን ውቅር በሚመለከት አብዛኛው ድምጽ እንዲኖራቸው የተደረገው ከፍርድ ቤቱ ራሱ የወጡ አካላትን ሆኖ ተጨማሪ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ለፍርድ ቤቱ እድገትና ተደራሽነት አስተጽኦ ያበረክታሉ ተብለው የሚገመቱ ሌሎችም አባላት እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡ በተለይም የአባላቱን ብዛትና ስብጥር በሚመለከት የፍርድ ቤቱ አጀንዳዎች በሶስተኛ ወገን እጅ እንዳይወድቁና አባላቱ በቁጥራቸው መብዛት ምክንያት ለውሳኔዎች ከተገቢው ጊዜ በላይ መውሰድ እንዳያስከትል ቀድሞ ታስበው የነበሩ በርካታ የባላድርሻ አካላት ተዋጽዖና የጉባዔው አባላት ብዛት ተሻሽሎ ዘጠኝ ለፍርድ ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ አካላት ብቻ የተሳተፉበት ጉባዔ እንዲሆን ተመርጧል፡፡

እነዚህም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት፣ አንድ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች ተወካይ፣ ሁለት የዑለማ ምክር ቤት አባል፣ አንድ የፌዴራል ፍርድ ቤት የረዥም ጊዜ ልምድ ያለው ዳኛ፣ አንድ የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል እና አንድ ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰብ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ሃያ ሶስት፡-

<u>የጉባዔው ስልጣንና ተግባርን በሚመለከት</u> ፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጉባዔ ከፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚለየው የዲሲፕሊንና የዳኞች መብትና ግዴታ የሚመለከት ተቋም ብቻ ሳይሆን የፍርድ ቤቱ የዳኝነት ስራ ላይ ብቻ ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት ሳይኖረው ለፍርድ ቤቱ ሁለንተናዊ እድገት የሚሰራ ጉባዔ እንዲሆን ታቅዶ መቋቋሙ ነው፡፡ በተለይም ከላይ የተገለጸውን የባለቤትን ኃላፊነት ወስዶ ፍርድ ቤቱን በማህበረሰቡ ዘንድ የማስተዋወቅ ተጨማሪ ድጋፍና በጀት የማፈላለግ፣ ለፍርድ ቤቱ ስራ የሚያግዙ የሽሪዓ ህግ ጥናትና ምርምርን የሚያሳልጥ፣ የሸሪዓ ህግ ኮዲፊኬሽን ስራን የሚያስተባብርና ሌሎችም የፍርድ ቤቱን ዘላቂ ህልውናና ጥንካሬ የሚያግዙ ተግባራትን እንዲያከናውን የተፈለገ ጉባዔ በመሆኑ ይህንን ኃላፊነት የሚመጥኑ ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች በሚቀረጹበት ወቅት ዋነኛ ትኩረት የተሰጠው የጉባዔው መቋቋም ከታለመለት ዓላማ ወጥቶ ፍርድ ቤቶቹ ላይና የዳኝነት ስራው ላይ ተጽዕኖ የማሳረፍ አቅም እንዳይኖረውና በተቃራኒው ግን ለፍርድ ቤቶቹና ለዳኞቻቸው ጥቅም እንዲሁም ለተገልጋዩ እርካታ የሚሰራ ተቋም ሆኖ ከዚህ በፊት የነበረውን የባለቤትነት ጥያቄ መቀረፉ ላይ ነው፡፡

አንቀጽ ሃያ አራት፡-

<u>የጉባዔው ስብሰባና አሰራርን በሚመለከት</u>፡ እንደማንኛውም ጉባዔ አስፈላጊ በመሆኑና የአባላቱን መብትና ግዴታም የሚያስቀምጥ በመሆኑ እራሱን የቻለ ድንጋጌ ተቀምጦለታል፡፡ ነገር ግን ዝርዝር የጉባዔው አሰራር በዚህ አዋጅ ስር ማስቀመጥ አዳጋች ከመሆኑ አንጻር ጉባዔው ከተቋቋመ በኋላ የራሱን የስብሰባ አመራር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

አንቀጽ ሃያ አምስት፡-

<u>የጉባዔው ጽ/ቤትና ሰራተኞችን በሚመለከት</u>፡ እንደ አንድ የራሱ የህግ ሰውነት ያለው ተቋም የእለት ተዕለት ስራውን የሚያከናውንበት የሰው ሀይልና መሰረተ ልማት እንደሚኖረው መደንገግ ያስፈልጋል፡፡ ጉባዔው ያሉበትን ኃላፊነትና ተግባራት ማከናወን እንዲችልና የጉባዔውን አስተዳደር የሚመሩት አካላትም መታወቅ ያለባቸው በመሆኑና ስራቸውን አውቀው መፈጸም እንዲችሉ ይህንን የሚያሳይ ድንጋጌ ተካቷል፡፡ በተጨማሪም ጉባዔው ጽ/ቤት

የሚኖረው ከሆነ እንደ ተቋም የሚመራው በጉባዔው ሰብሳቢና በጉባዔው ቢሆንም የጉባዔውን ውሳኔዎችና እቅዶች የሚያስፈጽምና መፈጸሙን የሚከታተል በቋሚነት ጽ/ቤቱን የሚያስተዳድር ዋና ጸሐፊ ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የጉባዔው ዋና ጸሐፊ እንደሚኖረው፣የሚሾምበት መንገድና ስልጣንና ኃላፊነቱን የሚደነግጉ ተጨማሪ ንዑስ አንቀጾች ተካተዋል፡፡

__አንቀጽ ሃያ ስድስት፡-__

__የጉባዔውን በጀት በሚመለከት__፡ እንደ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ በጀት ሁሉ ከፍርድ ቤቱ ጋር በጋራ አቅርቦ በማንና እንዴት እንደሚፈቀድለት የሚወስን ድንጋጌም ተቀምጧል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የጉባዔው አንዱና ዋነኛው ስራ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው ለራሱና ለሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ መንግስት ከሚወስነው በጀት በተጨማሪ በአዋጁ የተፈቀደውን ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ የበጀት እገዛ ማፈላለግ ነው፡፡

ስለዚህ ለዓመታዊ የስራ እቅዱ ብቻ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ለዳኞች የሚያስፈልገውን ስልጠና ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ፈንድ የማፈላለግ ኃላፊነትም ጭምር ይኖርበታል፡፡ የጉባዔውንም ሆነ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ በጀት የሚሸፈነው ከመንግስት በሚገኝ ድጎማ ቢሆንም ከሶስተኛ ወገኖች የሚገኝ ማንኛው ድጋፍ ፍርድ ቤቶቹን ነጻነት እንዳይጋፋ በጉባዔው ሲጸድቅ ብቻ መሆን እንዳለበት መደንገግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለቱም የበጀት ድንጋጌዎች ላይ ይህ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## __ክፍል ሰባት__

## __ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች__

በቀድሞው አዋጅ ቁጥር 188/1992 ስር አንዳንድ በልዩ ልዩ ድጋጌዎች ስር መቀመጥ የነበረባቸው ድጋጌዎች በተለያዩ አዋጁ ክፍሎች ስር ተሰባጥረው የነበረ በመሆኑ ይህንን በሚያርም መልኩ የልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ክፍል ተሻሽሎ ተቀርጿል፡፡

__አንቀጽ ሃያ ሰባት፡-__

__የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚሰሩባቸውን ህጎችን__፡ በሚመለከት የቀድሞው አዋጅ በሸሪዓው መሰረታዊ ህግ መሰረት እንዲወስኑ ቢያዝም የስነ ስርዓት ህጉን በሚመለከት ግን ዋናውን መርህ እንደ ልዩ ሁኔታ፤ ልዩ ሁኔታውን እንደ መርህ የሚስቀምጥ ነው፡፡

የሸሪዓ ህግ የራሱ የስነ ስርዓት ህግና የማስረጃ ህግ ያለው የህግ ስርዓት ከመሆኑ አንጻር በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉና በሸሪዓ ሕጉ መካከል አለመጣጠም በሚፈጠርበት ጊዜም ዳኞች መፈጸም ያለባቸውን የቀድሞው አዋጅ አይጠቁምም፡፡

ከዚህም አልፎ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ የራሱን ስነ ስርዓት ህግ መድብል ለማዘጋጀትና ለመጠቀም ከላይ እንደተገለጸው የሸሪዓ ህግ ስርዓቱ የራሱ የሆኑ የመሰረታዊ፣ የማስረጃና የስነ ስርዓት ህጎች ያሉት እንደመሆኑ ሙሉ ለሙሉ የመደበኛ ህጉን መሰረት አድርገው እንዲወስኑ ለሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ በህግ መደንገጉ አግባብነት የለውም፡፡

በርግጥ ለዚህ ምክንያቱ ከቀድሞው አዋጅ አቀራረጽ አንጻር በሁሉም ፍርድ ቤቶች የአሰራር ወጥነት እንዲሰፍን ለማድረግ ታስቦ ቢሆንም በአንድ ፍርድ ቤት ውስጥ ሁለት ዓይነት (ያውም እርስ በራሳቸው ሊጋጩ የሚችሉ ህጎችን) እኩል ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ከወጥነት ተቃራኒ የሆነ ውጤት ሊያስክትል እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡

ስለዚህ በመሰል ጉዳዮች ላይ አዋጁ ተሻሽሎ ቢያንስ በመርህ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ በሁሉም ጉዳዮች ላይ የሸሪዓ ህጉን መሰረት አድርገው መስራት እንዳለባቸውና መደበኛው የስነ ስርዓትም ሆነ የማስረጃ እንዲሁም ሌሎ ህጎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ከሸሪዓ ህጉ ጋር እስካልተጋጩ ድረስ ክፍተቶችን ለማሟያነት እንደሆነ በሚያሳይ መልኩ የተሻሻሉ አንቀጾች ተካተዋል፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ ስምንት</u>፡-

<u>**ፍርድ ቤትን ስለመድፈር**</u>፡ በሚመለከትም የቀድሞው አዋጅ አንቀጽ 7 ስር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተቀመጠው ስልጣን ያነሰ ስልጣን ለዳኞች ይሰጣል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ዳኛ በችሎት መድፈር ጥፋተኛ ያለውን አካል ወይም ግለሰብ መቅጣት የሚችለው ከብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) ያልበለጠ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር ያልበለጠ እስራት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 156(1)፣ 389 እና 481 እንዲሁም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 449(1)(ሀ) ከተሰጣቸው ለችሎት መድፈር ጠንከር ያለ ቅጣት የመጣል ስልጣን ጋር በተጣጣመ መልኩ መሻሻል ያለበት ሆኖ በመገኘት ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ</u>፡-

<u>**የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችና ትዕዛዞች አፈጻጸምን በሚመለከት**</u>፡ የቀድሞው አዋጅ ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ቢኖሩም በተግባር ከሚያጋጥሙ ችግሮች አንጻር ግን አንዳንድ

መሻሻል ያለባቸውና በማያሻማና ግልጽ ቋንቋ መቀመጥ ያለባቸው ድንጋጌዎች ይኖራሉ፡፡ በተለይም፤

አስፈጻሚ አካላት ፍርድ ቤቶቹ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት እውቅና ለሰጡት ወሳኝ ኩነት ሁኔታ ያለምንም ተጨማሪ ማስረጃ እውቅናና ምዝገባ መስጠት እንዳለባቸው፣

የፍርድ ቤቶቹም ዳኞች በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ያሏቸውን የፍርድ ማስፈጸሚያ አማራጮች በመጠቀም የፍርድ ባለመብቶችና ተገልጋዮች በፍርድ ቤቱ ያገኙትን ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ውጤት ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ስልጣንና ግዴታ ያለባቸው መሆኑንና የፍርድ ቤቶቹ ሬጅስትራሮችም ለፍርድ ቤቱና ለዳኞቹ ትዕዛዝ መፈጸም የሚጠበቅባቸውን ግዴታ መወጣት ያለባቸው መሆኑን በሚያሳይ መልኩ የተቀረጹ ድንጋጌዎች በአዋጁ ውስጥ ተካተዋል፡፡

<u>**አንቀጽ ሰላሳ**</u>፡-

<u>**የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድን በሚመለከት**</u>፡ አዋጅ ቁጥር 188/1992 ያለ ምንም የሸሪዓ ህግ ባለሙያ እገዛ የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞችን ዲሲፕሊን ክስና እርምጃ አወሳሰድ የመወሰን ስልጣን ተሰጥቶት የነበረ መሆኑ አንዱ ሊታረም የሚገባው አሰራርና ህግ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹን የፍትህ አካልነት በሚያረጋግጥና ከአቻ ፍርድ ቤቶ ባላነሰ ክብር ሊሰጣቸውና ትዕዛዛቸው ሊከበር የሚገባው መሆኑን በሚያመላክት መልኩ መሻሻል አለባቸው፡፡

ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ ስር የዲሲፕሊን ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የማን እንደሆነና ተፈጻሚነት ያላቸውን ህጎችም በግልጽ የሚያስቀመጥ ድንጋጌ መጨመር በማስፈለጉ ይህንን ክፍተት የሚሞሉ ንዑስ አንቀጾች ተጨምረዋል፡፡

<u>**አንቀጽ ሰላሳ አንድ**</u>፡-

<u>**የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**</u>፡ ሁለት ንዑስ አንቀጾች ሲሆኑ በድሬዳዋና በአዲስ አበባ በሚገኙ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እስከ አሁን እየታዩ ያሉ ጉዳዮች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተከፈቱ እንደሆነ በነበሩት እንደሚቀጥሉ ከመደንገግ ውጪ ሌላ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ መጨመር አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**አንቀጽ ሰላሳ ሁለት**

**የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በጀት፡** ይህም ድንጋጌ ከላይ ለጉባዔው በተቀመጠው መልኩ ተሻሽሎ ከመንግስት ውጪ የሚገኙ ድጋፎች በቅድሚያ በጉባዔው መጽደቅ እንዳለባቸው የሚደነገግ ሀረግ ተጨምሮበታል፡፡

**አንቀጽ ሰላሳ ሶስት**

**ስለ ዳኝነት ክፍያ፡** የፌዴራል ሸሪዓ ፍድ ቤቶ ላይ ይነሱ ከነበሩ ወቀሳዎች አንዱ ፍርድ ቤቶቹ እራሳቸውን የሚስችልም ሆነ ለወጪያቸውና ለበጀታቸው ድጎማ የሚሆን የዳኝነት ክፍያ ስርዓት አልነበራቸውም የሚለው ነው፡፡ ይህንንም ለማሻሻል የፌዴራል ፍርድ ቤቶ የዳኝነት ክፍያን በሚመለከት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አከፋፈል ደንብ ድጋጌዎች መሰረት ተፈጻሚ እንደሚሆን መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**አንቀጽ ሰላሳ አራት**

**ስለተሻሩ ህጎች፡** የሚደነግገው አንቀጽም ከላይ እንደተገለጸው ከማሻሻያ ድንጋጌዎች ይልቅ አዲስ አዋጅ ማርቀቅ የተመረጠ በመሆኑ የቀድሞው አዋጅና ሌሎች አሰራሮች እንደተሻሩ ይደነግጋል፡

**አንቀጽ ሰላሳ አምስት፡-**

አዋጁም የሚጸናው ወይም ተፈጻሚ የሚሆነው በነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት እለት አንስቶ መሆኑም ተደንግጓል፡፡ ይህ በአሁኑ ሰዓት የተለመደ አሰራር እየሆነ ከመምጣቱም በላይ ፍርድ ቤቶቹም አዋጁ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ አስፈላጊውን የተቋም ማሻሻያ ክንውኖች እንዲያጠናቅቁ ጊዜ የሚሰጣቸው ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደሞከርነው አሁን በሥራ ላይ ያለውና ረዥም ጊዜ ያስቆጠረው አዋጅ ቁጥር 188/1992 ሊሻሻል የሚችልበት፣ የሚገባበትና ግድ የሚልባቸውን ምክንያቶች ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥን ሲሆን የተቀመጡት አመክኒዮዎች የረቂቅ አዘጋጅ ኮሚቴው ባከናወነው የዳሰሳ ጥናት፣ የኮሚቴው አባላት የበርካታ ወራት ስብሰባዎች ውይይት፣ ከባለሙያዎችና ከእምነቱ ምሁራን ጋር በተደረገው የጋር ውይይትና ትችት እንዲሁም ከኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴርና ከፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ እንዲሁም ጉባዔው ካቋቋመው ልዩ ኮሚቴ የተገኙ ገንቢ አስተያቶችንም ጭምር ከግምት ውስጥ በማስገባት የተደረሰበት ድምዳሜ ነው፡፡ ከዚህ የሀተታ ዘምክንያት ሰነድ በተጨማሪ ኮሚቴው በሚያከናውናቸው ውይይቶች የያዛቸው ቃለ ገባዔዎች፣ የጥናቱ ሰነድ፣ ለጥናትና ምርምር ኮሚቴው የተገለገለባቸው ሰነዶች በሙሉ የተሻሻለው ረቂቅ አዋጅ ድንጋጌዎች በዝግጅት ወቅት ያሳለፉትን ሂደቶች የሚያሳዩና የአዋጅ መሰናዶች አካል የሆኑ መዛግብት ናቸው፡፡ ስለዚህ የረቂቅ አዋጁን ድንጋጌዎች ለመረዳት ይህ ሰነድ እንደመነሻ ያገለግላል እንጂ በውስጡ የተገለጹት አመክኒዮዎች የማሻሻያዎቹ ብቸኛ ምክንያቶች እንዳልሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

# <u>አዋጅ ቁጥር ……../2018</u>

## <u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት እንዲሁም አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የግል እና የቤተሰብ የሕግ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚነሱ አለመግባባቶችን በፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ በባህላዊና በሃይማኖት ሕጐች ለመዳኘት የሚቻል በመሆኑ፤

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች እነዚህን ተቋማት በሌሉ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ እንዲያቋቁሙ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሀገራችን ተቋቁመው የሚገኙ በመሆኑ፤

የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እንደ አንድ የሀገራችን የፍትህ አካል የዳኝነት ነጻነታቸው፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር መዘርጋታቸው፣ ቀልጣፋና ተደራሽነት ያለው የዳኝነት አገልግሎት መስጠታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለፍርድ ቤቶቹ ዘለቄታዊ እድገትና ጥንካሬ የሚሰራ የፍርድ ቤት አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋምና የፍትህ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋታቸውን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፻፹፰/፲፱፺፱ ከጸደቀበት ከሩብ ምዕተ ዓመት በላይ ያለፈና በዚህ ጊዜ ውስጥ የተከናወኑ የህግ ማዕቀፍ ለውጦችና ነባራዊ ሁኔታዎችን ባገናዘበ የተሻሻለ አዋጅ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፸፰(፭) እንዲሁም አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ……../…….. " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩ "ዳኛ" ማለት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ተሹሞ የሚሠራ ዳኛ ነው፡፡

፪ "ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት" ማለት እንደየቅደም ተከተላቸው የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ነው፡፡

፫ "ተጠሪ ዳኛ" ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎቶች ኃላፊዎች ሆነው የየምድብ ችሎቶቻቸውን ሥራ የሚመሩ ዳኞች ናቸው፡

፬ "የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች" ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ናቸው፡፡

፭ "የሥነ ሥርዓት ሕጎች" ማለት በዚህ አዋጅ ስልጣን በተሰጠው አካል የሚወጡ ሸሪዓውን መሰረት ያደረጉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስነስርዓት ህጎች፣ በአሁኑ ወቅት በፍርድ ቤቶቹ በስራ ላይ የሚገኘውን በ፲፱፻፶፭ የወጣው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግና ማሻሻያዎቹን ይጨምራል፡፡

፮ "ጉባዔ" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባኤ ነው፡፡

፯ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፫/፪ሺ፲፫ የተቋቋመው ጉባኤ ነው፡፡

፰ "የአስተዳደር ሠራተኛ"  ማለት ከዳኛ፣ ረዳት ዳኛ፣ ሬጅስትራርና ሌሎች በጉባዔው በሹመት ከሚመደቡ ሰራተኞችና ኃላፊዎች ዉጭ ያሉ ሁሉንም የሸሪዓ ፍርድ ቤትና አስተዳደር ጉባዔው ሰራተኛን ያጠቃልላል፡፡

፱ "መሰረታዊ የሸሪዓ ህግ አተረጓጎም ስህተት" ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሸሪዓ ህግ ስህተት ያለበትና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯(፫) መሰረት በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችል የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ፣

ሀ) የሸሪዓ ህግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው የሸሪዓ ህግ ምንጭ የሚጠቅስ፤

ለ) በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚችል አንድን ጉዳይ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ በማድረግ የተሰጠ፤

ሐ) በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፤

መ) ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ወይም

ሠ) ከፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር በመቃረን የተሰጠ፤

የመጨረሻ ውሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ነው፡፡

## ፫ መቋቋም

፩ ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፤

፪ ተጠሪነታቸው ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁመዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለ ፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የወል ዳኝነት ስልጣን

## ፬ መሠረቱ

፩ በፌዴራል መንግስቱ ህጎች በፌዴራል መንግስቱ ስልጣን ስር መሆናቸው በተገለጹ ባለጉዳዮችና ቦታዎች የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከዚህ በታች በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ የወል የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፤

ሀ) ጥያቄ ያስከተለው ጋብቻ በሸሪዓ ህግ መሰረት የተፈጸመ የሆነ እንደሆነ ወይም ባለጉዳዮቹ በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ፈቅደው ከሆነ፤ ማናቸውም የጋብቻና የጋብቻ ውጤት፡ የፍቺና የፍቺ ውጤት፡ የቀለብ አወሳሰን፡ አካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት አስተዳደግና ሞግዚትነት ወይም በቤተሰብ ተዛምዶ እንዲሁም የህግ ችሎታ ያጡ ሰዎች ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን አስመልክቶ፣

ለ) የወቅፍና የወቅፍ አስተዳደር (ናዚርነት)፣ የስጦታ (ሂባ)፣ የውርስ፣ ውርስ ማጣራትና ውርስ ሀብት ክፍፍል፣ ወይም የኑዛዜ ጉዳዮችን በተመለከተ አውራሽ ወይም ስጦታ አድራጊ ወይም ተናዛዥ ሙስሊም የሆነ እንደሆነ ወይም ሟች በሞተበት ሰዓት ሙስሊም ሆኖ የሞተ እንደሆነ፣

ሐ) በግልጽ የሸሪዓ ህጉን መሰረት አድርገው የተመሰረቱ ስምምነቶችና ግንኙነቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ-ሐ) በተገለጹት ጉዳዮች ላይ በሚቀርቡ ክሶች ጋር ተያይዞ የሚሰጡ ፍርዶችና ውሳኔዎች አፈጻጸምና ወጪና ኪሣራ መወሰንን በተመለከተ፣

ሠ) በውጪ ሀገር የሞተ/ሞተች ሙስሊም ኢትዮጵያዊ/ዊት የቀብር ስነ ስርዓት እንዲፈጸም የሚሰጥ ፍቃድንና የጋብቻ ስነ ስርዓትን የሚያከናውኑ የሸሪዓ አጋቢዎች ፍቃድ መስጠትና መሻር፣

፪ በዚህ አንቀጽ ስር በተገለፁት ጉዳዮች ላይ ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ሥልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፍቃደኝነታቸው ከዚህ በታች በአንቀጽ ፭ በተደነገገው መሰረት የተረጋገጠ ከሆነ ብቻ ይሆናል፡፡

__፭ ስለ ፍቃደኝነት አሰጣጥ ወይም አገላለጽ__

፩. በሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ተከራካሪዎች በፍርድ ቤቶቹ ለመዳኘት ፍቃደኝነት ተገኝቷል የሚባለው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ የወል የዳኝነት ስልጣን በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት አቤቱታ አቅርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆኑን በመጀመሪያው ቀጠሮ ያሳወቀ እንደሆነ ነው፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስር የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ የደረሰዉ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩ በሸርዓ ፍርድ እንደሚዳኝ እያወቀ በመጀመሪያ ቀጠሮ

ቀን ያልተገኘ እንደሆነ ወይም በስነ- ስርዓት ህጉ መሰረት ጉዳዩ እንዲ ተከራካሪ ወገን በሌለበት እንዲቀጥል የተወሰነ እንደ ሆነ ፍቃድ እንደ ተገኘ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

፫. ግንኙነቱ በተመሰረተበት ውል ወይም ማንኛውም ስምምነት ላይ ግራ ቀኙ ከውሉ/ከስምምነቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶች በሸሪዓ ህጉ ወይም በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ እንደሚዳኙ በግልጽ ያስቀመጡ እንደሆነና ጉዳዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር የሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው ጉዳዩ ከሆነ በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ እንዲታይ ፍቃድ እንደተገኘ ይቆጠራል፡፡

፬. በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ተከራካሪ ከሆኑ ወገኖች መብት የመነጨለት ተተኪ ባለጉዳይ በመታየት ላይ ባለው ጉዳይ ላይ ፍቃደኝነትን መሰረት አድርጎ መቃወሚያ ለማንሳት አይችልም፡፡

፭. የሶስተኛ ወገን ተከራካሪዎችን ፍቃደኝነት በሚመለከት፡-

ሀ. በሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይቶ በተወሰነ ወይም በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ የተሰጠው ወይም ሊሰጥ የሚችለው ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መብትና ጥቅሜን ይነካል የሚል ወገን በስነ ስርዓት ህጉ መሰረት በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፍቃደኛ አለመሆኑንም በግልጽ እስካላመለከተ ድረስ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ መብትና ጥቅሙ የሚነካ መሆኑን አረጋግጦ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ከወሰነ በኂላ፤

ለ. በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የታዘዘ ሶስተኛ ወገን ለክርክሩ በሚያቀርበው አቤቱታ ጽሁፍ፣ መከራከሪያ ጽሁፍ ወይም ማመልከቻ ላይ በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፍቃደኛ አለመሆኑንም በግልጽ እስካላመለከተ ድረስ፤

ፍቃደኝነትን መሰረት አድርጎ መቃወሚያ ለማንሳት አይችልም፡፡

፮. በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደሌለው በመግለጽ መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎቹን ያሠናብታል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን</u>

### <u>፮ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣንና የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ውጤት</u>

፩ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ሀ) ከአንድ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎት ወደ ሌላ የፌደራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲዘዋወር በሚቀርብ ጥያቄ ላይ፤ እና

ለ) በክልልና በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ወይም በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች መካከል የሚነሳ የዳኝነት ስልጣን በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ፡፡

፪ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ሀ) የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች፤ ወይም

ለ) የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮችን፤

፫. በተጨማሪም የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ሲሆን ችሎቱም፡-

ሀ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ዓይቶ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ወይም የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ አይቶ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ፤

ለ) የክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ስልጣን ያለው ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ፤ ወይም

ሐ) የሸሪዓ ህግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው የሸሪዓ ህግ ምንጭ የሚጠቅስና በሀገር ደረጃ ወጥ የሆነ የሸሪዓ ህግ አተረጓጎም እንዲኖር የሚረዱ ጉዳዮች ላይ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የሸሪዓ ህግ ትርጉም ጋር ተቃርኖ የተወሰነ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ፤

የተፈጸመ መሰረታዊ የሸሪዓ ህግም ሆነ ወይም የስነ ስርዓት ህጎች አተረጓጎም ስህተት አለበት ተብሎ ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል፡፡

፬. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው መሰረታዊ የሸሪዓ ህግ ወይም የስነ ስርዓት ህጎች ትርጉም በሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይተው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻው ውሳኔ ሲሆን ውሳኔው ከተሰጠበት እለት አንስቶ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የሀገሪቱ የፌዴራልም ሆነ የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

፭ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎቶች አስገዳጅ ህግ ትርጉም የተሰጠባቸው ውሳኔዎች በኤሌክትሮኒክስ ወይም በህትመት ሚዲያዎች በተቻለ ፍጥነት ያሰራጫል፡፡

፮ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተደራጅቶ ወደ ስራ እስከሚገባበት ጊዜ ድረስ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በባለጉዳዮች ጠያቂነት በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ችሎቶች መካከል መሰረታዊ የትርጉም ልዩነት ያለባቸው የሸሪዓውን ህግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲነሱ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው እንዲያዩት ለማድረግ ይችላል፡፡

፯ በፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግን መሰረት አድርገው በሰጡት የመጨረሻ ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ላይ የሥነ ሥርዓት ህግ አተረጓጎም መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞብኛል በሚል ተከራካሪ ወገን አመልካችነት በቀረበ የሰበር አቤቱታ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አይቶ ተፈጸመ በተባለው የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ህግ ግድፈት ላይ ተገቢው የመወሰን ስልጣን አለው፡፡

## <u>፮ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ስልጣን</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖሩታል፡፡

፩ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግምታቸው ከብር ፲ ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን ብር) በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

፪ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፫ አንድን ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር የሚቀርብን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ፰ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግምታቸው እስከ ብር ፲ ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) የሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯(፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ግምታቸው በገንዘብ ሊተመን በማይችሉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አራት

## የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሰራር

## ፱ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች፣ ዳኞችና ሌሎች ሰራተኞች

፩ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዝዳንት እና አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞችና ሬጅስትራሮች ይኖሩታል፡፡

፪ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፲ የፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች

የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለየፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንት፣ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ተጠሪ ዳኞች፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች፣ ሬጅስትራሮች እንዲሁም ሌሎች ሠራተኞች ይኖሯቸዋል፡፡

## ፲፩ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ችሎትና የማስቻያ ስፍራ

፩ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአንድ ዳኛ ያስችላሉ፡፡

፪ በፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎቶች አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ተሰይመው ያስችላሉ፡፡

፫ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ማስቻያ ስፍራ አዲስ አበባ ይሆናል ፡፡

፬ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የማስቻያ ስፍራ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ይሆናል።

፭ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የተገልጋዩን ማህበረሰብ ብዛት እና የፍርድ ቤቶቹን በጀት ባማከለ ሁኔታ ተጨማሪ ምድብ ችሎቶች ይኖሯቸዋል።

## ፲፪ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ

፩ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ የፌዴራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ ይሆናል።

፪ የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ለማይችል ባለጉዳይ ፍርድ ቤቱ አስተርጓሚ ይመድብለታል።

## ፲፫ በግልጽ ችሎት ስለማስቻልና ከችሎት ስለመነሳት

፩ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስችላሉ።

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም የተከራካሪዎችን የግል ህይወት፣ የህዝብ ሞራል ሁኔታ ወይም ግብረገብነትን ለመጠበቅ በሸሪዓ ህጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቶቹ በዝግ ችሎት ያስችላሉ።

፫ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል።

፬ ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ የሚነሳበትን ምክንያትና ሁኔታ እንዲሁም ማመልከቻው ስለሚያስከትለው ኪሳራና ቅጣት በተመለከተ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ሸሪዓ ህጉን መሰረት አድርጎ የሚያወጣው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስነ ስርዓትና አሰራር ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ላይ ከሸሪዓ ህጉ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ አግባብነት ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፭. ከላይ የተመለከቱት የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዳኛው በችሎት ላይ ሊቀመጥ የማይገባው መሆኑን በራሱ ሲያውቅ ከችሎት ተነስቶ ሌላ ዳኛ እንዲተካ ይደረጋል፡

## ክፍል አምስት

### የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች መስፈርትና አሿሿም

### ፲፬ ዳኛ ሆኖ ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች

፩. የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ማንኛውም ሙስሊም ኢትዮጵያዊ በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል፡፡

ሀ) በእስልምና ትምህርት ተቋማት በሸሪዓ ሕግ የሠለጠነ ወይም በሸሪዓ ሕግ በቂ የሆነ ልምድና ዕውቀት ያካበተ፤

ለ) በታታሪነቱና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤

ሐ) የወንጀል ሪኮርድ የሌለበት ወይም ከዚህ በፊት ከየትኛውም ተቋም በስነምግባር ጉድለት ያልተሰናበተ፤

መ) የየትኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፤

ሠ) ዳኛ ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ፤ እና

ረ) ዕድሜው ከ፳፫ ዓመት በላይ የሆነ፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስር የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ለፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ወይም ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚወዳደር ዳኛ በሸሪዓ ፍርድ ቤት በዳኛነት ያገለገለበት እንደ ስራ ልምድ ይያዝለታል፡፡

፫ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኝነት መስፈርቶችና የምልመላና አመራረጥ አሰራርን የሚደነግግ መመሪያ ያወጣል፡፡

### ፲፭ የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች እና ዳኞች አሿሿም

፩ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የዳኞችን ምልመላ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ድንጋጌዎች መሰረት ያከናውናል፡፡

፪ ጉባዔው የተመለመሉትን ዕጩ ዳኞችን አጭር የሕይወት ታሪክ መግለጫ አዘጋጅቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በማቅረብ ሹመታቸው እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

፫ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች እና ዳኞች ሹመት የሚጸድቀው፣

ሀ. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ሹመት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን፣

ለ. የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች እና የሌሎች በየትኛውም ደረጃ የሚመደቡ ዳኞች ሹመት በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡

**<u>፲፯ ስለ ዳኞች ደሞዝ፣ ጥቅማጥቅምና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች</u>**

በዚህ አዋጅ መሰረት ለተሾመ ማንኛውም ዳኛ የፌዴራል ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ አዋጅ ስለ ዳኞች የስራ ዘመን፣ ያለመከሰስ መብት፣ የደረጃ እድገት፣ ዝውውር፣ እረፍት፣ የምርምር ስራ ተሳትፎ፣ ስልጠና፣ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ የስራ ስንብትና ሌሎችም ጉዳዮች የተደነገጉ ድንጋጌዎች በሙሉ ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳኞችም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለ ፕሬዝዳንቶች ምክትል ፕሬዝዳንትና ተጠሪ ዳኞች አሿሿም፣ ስልጣንና ተግባር</u>

**<u>፲፮ ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

፩. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በፍርድ ቤቱ አስተዳደር ጉባዔ እና በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ትብብር ተመልምለው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ አንድ ፕሬዝዳንትና አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት ይኖሩታል፡፡

፪ የፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ መልኩ የሚመለመሉና በጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሰየሙ አንድ፣ አንድ ፕሬዝዳንት ይኖራቸዋል፡፡

፫. ከምድብ ችሎቶችና የፍርድ ቤቶቹ ስራ ብዛት አንጻር እንደ አስፈላጊነቱ ለፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ምክትል ፕሬዝዳንቶችና የምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኞች ሊኖሯቸው ይችላል።

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት የሚሾሙ ምክትል ፕሬዝዳንቶች በጉባዔው ተመልምለው በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት የሚሾሙ ሲሆን የምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኞች በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በጉባዔው የሚሾሙ ይሆናል።

፭. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት የሚሾሙት ላልተወሰነ ጊዜ ሲሆን ከጉባዔው 1/3ኛ በሚሆኑት አባለት ጥያቄ በ2/3ኛ ድምጽ ተወስኖ በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ በማንኛውም ጊዜ ከኃላፊነታቸው ሊነሱ ይችላሉ።

<u>፲፰ የፌዴራል ጠቅላይ  ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባር</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፡-

፩ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን በበላይነት ያስተዳድራል፣

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዝዳንቱ

ሀ) በየደረጃው ያሉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን መዋቅር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድለት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በዚህ አዋጅ ለፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ የተሰጡ ስልጣንና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ዳኞችን፣ የፌዴራል ጠቅላይና ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች  ሰብሳቢ ዳኞች፣ ለፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ዳኞችን እንዲሁም ሌሎች ተሿሚዎችን በየደረጃው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውስጥ በመደልደል ያሠራል፤

ሐ)   የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ደልድሎ ያሰራል፣ ያሰናብታል፤

መ)   በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫(፲፪) መሰረት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች ቀጣይነት ያለው ስልጠና ማግኘታቸውን ይከታተላል፤

ሠ) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ሰራተኞችን የሚመለከቱ ህጎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫(፰) መሰረት የተደነገጉ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰራተኞች የአሰራር ስነ ስርዓቶችን ተፈጻሚ መሆናቸው ይከታተላል፤

ረ) የፍርድ ቤቶቹንና የጉባዔውን የስራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እቅድና በጀት ለኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመቅረቡ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት በማቅረብ በኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲፈቀድለት በሥራ ላይ ያውላል፤

ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ መሰረት ለፍርድ ቤቱ በመንግስት ከሚገኘው በጀት በተጨማሪ ለፍርድ ቤቶቹ የሚያስፈልጋቸውን የበጀት ድጋፍ ከጉባዔው ጋር በመተባበር ያፈላልጋል ጉባዔው ድጋፉን ለመቀበል ፈቅዶ ሲያጸድቅለትም ስራ ላይ ያውላል፤

ሸ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤትን ፋይናንስ ያስተዳድራል፤

ቀ) የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስላከናወኗቸው ስራዎች አፈፃፀም በቋሚነት በየሩብ ዓመቱ

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤

በ) የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን እና የጉባዔውን የስራ አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀም ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ከማቅረቡ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ያቀርባል፤

ተ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤትን በመወከል አስፈላጊ ቦታዎች ላይ ይገኛል፤ መግለጫዎችን ይሰጣል፤

ቸ) ሌሎችም በዚህ አዋጅ የተሰጡትንና ከፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ የሚሰጡትን ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**<u>፲፱ የምክትል ፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ፕሬዝዳንቱ፡

፩ በፕሬዝዳንቱ የሚመሩለትን ጉዳዮች ያከናውናል፣

፪ ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱን ተክቶ ይሠራል፡፡

**<u>፳ የፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች ስልጣንና ተግባር</u>**

የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶች፡-

፩ ፍርድ ቤቶቻቸውን ይወክላሉ፤

፪. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የየፍርድ ቤቶቻቸውን ሥራ ይመራሉ፤

፫ የየፍርድ ቤቶቻቸውን ፋይናንስ ያስተዳድራሉ፤

፬ የየፍርድ ቤቶቻቸውን የአስተዳደር ሠራተኞች ያስተዳድራሉ፤

፭ ስለተከናወኑ ሥራዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በስታትስቲክስ የተደገፈ መግለጫ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፤

፮ ስለ ሥራዎቻቸው እንደ አስፈላጊነቱ ከጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ጋር በመመካከር ያከናውናሉ፤

፯ ሌሎችም በሕግና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የሚሰጧቸውን ህጋዊ ተግባራት ያከናውናሉ።

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ</u>

**<u>፳፩ መቋቋም</u>**

፩ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪ ጉባዔው የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ነው።

**<u>፳፪ ስለጉባዔው አደረጃጀት</u>**

፩ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

ሀ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፤

ለ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፤

ሐ) የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት፤

መ) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንድ ተወካይ፤

